# Case Reports

Note

The case reports part contains selected decisions of Ethiopia's Federal Supreme Court Cassastion Bench. The purpose of reporting the cases is to make them knwon to members of the legal profession. In this issue, three interesting decisions (i.e. *Ethiopian Mineral Development SC v GTT Trading*, *Dragados J & P Joint Venture v Saba Construction PLC*, and *National Mineral Corporation PLC v Dani Drilling PLC*) shaping the jurisprudence of Ethiopian law on arbitration are included.

In selecting a particular judgment for publication the Editorial Committee is not implying that the judgments are defective on any proposition or that it contains erroneous propositions. The cases are chosen for the interesting issue(s) of law they raise.

የሰ/መ/ቁ. 42239

ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
ሒጎስ ወሴደ
ተሻገር ገ/ሥሊሴ
በላቸው አንሺሶ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡-ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃላ.የተ. የግል ኩባንያ

ተጠሪ፡- ዲኒ ድሪሊንግ ኃላ.የተ.የግል ኩባንያ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የወርቅ ማዕድን ፍለጋ የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ውል ስምምነትን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ የተቋቋመው የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ/ም በሠጠው ውሣኔ አመልካች ለተጠሪ ብር 579,450.35(አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር ከሠላሣ አምስት ሣንቲም) እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ አመልካች በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 351 መሠረት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታኅሣስ 17 ቀን 2001 ዓ/ም በፃፉት አራት ገፅ የሠበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሣኔ በፍሬ ነገር እና በሕግ ረገድ ተፈፀሙ የሚሏቸውን ስህተቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ በራሱ አነሳሽነት ውሉን ባቋረጠበትና ዉሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ስራ ለፈታበት ሰላሳ አምስት ቀናት ብር 700,000. 00 ቅጣት አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ የውልም ሆነ የሕግ መሠረት የሌለው መሆኑን፣የግልግል ጉባኤ ዳኝነቱን የመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 317(1) ስር በተመለከተው ሣይሆን ከዚህ ውጪ ተገቢውን ጭብጥ ሣይዝ መሆኑን፣ውሣኔው በፍትሐ ብሔር ሕጉ የተመለከቱትን የውል አተረጓጓም ድንጋጌዎች ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑን፣ተጠሪ በወቅቱ ማስጠንቀቂያ ባልሰጠበት ሁኔታም ቅጣት መጠየቅ እንደማይችል፣ተጠሪ ውል አልተፈፀመልኝም የሚል እንደመሆኑ መጠን ሊደርስ የሚችለውን ኪሣራ ለመቀነስ በሕጉ ግዴታ ያለበት ሲሆን ጉዳት ሳይደርስበት ቅጣት እንዲከፈለው መጠየቁ ያላግባብ መሆኑንና በውሉ ላይ ዓይነተኛ መጣስ የሌለ ስለሆነ ውል እንዲፈርስ ዳኞች ውሣኔ ማሳለፍ እንደማይችለ፣እንዲሁም በጉዳዩ የተሠጠው ውሣኔ የቀረቡትን ማስረጃዎች በሚገባ

ያልመዘነ መሆኑን በሰፊው በመዘርዘር የግልግል ዳኞችና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሣኔ በማስረጃ ምዘናም ሆነ በህጉ አተረጓጎም እንዲሁም አፈጻጸም ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ሊሻር ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ጠበቃው መጋቢት 01 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገፅ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ የመልሱ ይዘትም የጉባኤው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን 23-05-1998 ዓ/ም ግራ ቀኙ በፈፀሙት ውል የተስማሙ መሆኑን ገልፀው ለሠበር ችሎቱ የሠበር አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለሆነ በዚህ ምክንያት ችሎቱ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ እንዲያደርግ፣ይህን የሚያልፍ ከሆነም ለአቤቱታው መሠረት የሆኑት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ክርክሮች ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ ውድቅ ሊደረጉ ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው የሠበር ችልቱ ጉዳዩን ለማየት ሕገ-መንግስታዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን በመዘርዘር የተጠሪ ጠበቃ መቃወሚያ የሕግ መሠረት የለውም በማለት የተቃወሙ ሲሆን ሌሎች ነጥቦችን በተመለከተም የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር መጋቢት 18 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈት የመሌስ መሌስ ማመሌከቻ ተከራክረዋሌ፡፡

የጉዲዩ አመጣጥ አጠር ባሇመሌኩ ከሊይ የተመሇከተው ሲሆን ይህ ችልትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካሊቸው የሔግ ዴንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተሇው መሌኩ መርምሮታሌ፡፡ እንዯመረመረውም የችልቱን ምሊሽ የሚያስፇሌጉት አበይት ጭብጦች፡-

1ኛ/ ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሠረት አመልካች ቅሬታውን ለሠበር ችሎት ለማቅረብ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም?፣

2ኛ/ አመልካች ለሰላሳ አምስት ቀናት የጉዳት ካሳ ለተጠሪ እንዲከፍል ተብሎ የተወሰነው የውሳኔ ክፍል በግራ ቀኙ መካከሌ በተደረገው ውል መሰረት አመልካች ግዴታውን ስለአለመወጣቱ ተጠሪ አስረድቶ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ሲሆን ሌሎች ነጥቦች በዚሁ ጭብጥ ስር እልባት ሊያገኙ የሚችሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## 1.የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

ይህን ጭብጥ ለመመለስ በአገራችን ውስጥ የሰበር ስርአት እና ስለአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎች አላማና በሕጉ ያላቸውን ማእቀፍ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

የሰበር ስርዓት አይነተኛ አላማ ከሆኑት አንዱ በአንድ ሀገር ውስጥ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጎጎም እና አፈጻጸም(Uniform interpretation and application of the law) መኖሩን ማረጋገጥ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሰበር ሥርዓት የሕግ የበላይነት ማረጋገጫ ዘዴ ነው ተብሎም ሊታሰብ የሚችል ነው፡፡ የሕግ የበላይነት በሰበር ሥርዓት ሊከበር ወይም ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ ጥራት፣ወጥነት ያለው ፍርዴ/ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት በሰጡት ውሳኔ ላይ የዳኝነት አካሉ በራሱ ዳኝነታዊ ቁጥጥር(Judicial Control) ሲኖረው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተመሳሳይ ጉዳዮች በተመሳሳይ መንገድና ሁኔታ ማየትን የፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓት የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የፍትሕ መሰረቱ ተመሳሳይ ጉዳዮችን በተመሳሳይ መንገድ ማስተናገድ ነው ተብሎም ይታሰባል፡፡ ይህ የሚተገበረውም አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም ፖሊሲዎች በትክክልና በወጥነት ሲተረጎሙና ሲፈጸሙ ነው፡፡ ወጥነትና

ትክክለኛነት ያለው የሕጎች አተረጓጎምና አፈፃፀም መኖሩ የሚረጋገጠው ደግሞ በዳኝነት አካለ በመጨረሻ ደረጃ በሚገኝ በሰበር ተቋም ነው፡፡

ሌላው ጉዳይ የሕጎች ወጥነት ያለው አተረጓጎምና አፈፃፀም መኖር የዜጎችን በሕግ ፊት እኩል የመሆን መብት የሚጠብቅ መሆኑ የሚታመን ሲሆን የዳኝነት አካሉ የዜጎችን በሕግ ፊት እኩል የመሆን መብት የማክበርና የማስከበር ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ደግሞ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 13(1)፣ 25 እና 85(1) ድንጋጌዎች ስር ከአስፈረው ሁኔታ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የሰበር ሥርዓት ይህንኑ ግዴታ የዳኝነት አካሉ የመወጣቱን ሁኔታ የሚቆጣጠርበት መሆኑም የሚታመን ነው፡፡ ሌላው በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ተቀባይት ያለው ጉዳይ የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ ሊቆይ የማይገባው ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዲቆይ ማድረግ በዳኝነት አካሉ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ያስከትላል፡፡ ምክንያቱም የሕግ ስህተት ያለበትን ውሳኔ ጸንቶ እንዲቆይ ማድረግ ሕብረተሰቡ በዳኝነት አካሉ እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ ነውና፡፡ በመሆኑም የሰበር ሥርአት የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዲይቆይ በማድረግ የዳኝነት አካሉ በሕብረተሰቡ ዘንድ የሚታመን፤ከበሬታ የተቸረው እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው የሰበር ሥርአት ለሕግ ስርዓቱ፣ለዳኝነት አካሉና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ ተብሎ የሚቋቋም መሆኑን ነው፡፡ ይህ ስርአት በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ውስጥ ተካቶ ለረዥም ጊዜያት ሲሰራበት የቆየ ሲሆን በ1987 ዓ/ም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት በአንቀፅ 83 ስር ተመልክቶ ከመገኘቱም በላይ ዝርዝሩ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አዋጅ ቁጥር 454/97 የተደነገገለት ሥርዓት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት በአንቀፅ 80 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ስር የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለው ሲደነግግ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ደግሞ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልል ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል ሲል ደንግጓል፡፡ ህገ-መንግስቱ በፌዴራልና በክልል ጉዳዮች የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያላቸውን ፍርድ ቤቶች ለይቶ ካስቀመጠ በኋላ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስልጣን ያለው መሆኑን በአንቀጽ 80(3(ሀ)) ስር ደንግጓል፡፡ ሰበር ችሎት ይህ ስልጣን የተሰጠው ከላይ የተመለከቱትን አላማዎች ለማሳካት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ በተለይ አዋጅ ቁጥር 454/1997 ሲታይ ከአምስት ያላነሱት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጥ የህግ ትርጉም ይኸው ችሎት ራሱ በሌላ ጊዜ እስካልለወጠው ድረስ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት ላይ የአስገዳጅነት ኃይል(Precedence) ያለው ስለመሆኑ በአንቀፅ 2(4) ስር አስቀምጧል፡፡ ይህም የሰበር ስርዓት በዳኝነት ስልጣን ተዋረድ በመጨረሻ እርከን ላይ ሆኖ ህጎች በትክክልና በወጥነት መተርጎማቸውንና መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ለተከራካሪ ወገኖች ጥቅም ወይም መብት ብቻ ሳይሆን ለዜጎች ጥቅም ተብሎ የተዘረጋ ሥርአት ወይም አሰራር መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ሰበር ህጋዊ ያልሆኑ ውሳኔዎች የሚሰበሩበት ወይም ጸንተው እንዲይቆዩ የሚደረግበት ሥርአት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ሰበር መደበኛ የይግባኝ ማቅረቢያ አሰራር ሳይሆን ፍርድ ቤቶች በውሳኔዎቻቸው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈጽመዋል በሚባልበት ልዩ ሁኔታ ብቻ የህጉ አተረጓጎም ወይም አተገባበር የሚቃናበት ወይም የሚታረምበት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህም ሥርአት የህግ አንድ ወጥ አተረጓጎምና አፈፃፀም በፍርድ ቤቶች ሁሉ ይረጋገጣል፡፡

ወደ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች አላማ ስንመለስ ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የመስማማት መብት ያላቸው መሆኑን ያሳዩናል፡፡

የግልግል ዳኝነት የሚቋቋምበት አይነተኛ አላማ ተካራካሪ ወገኖች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት በመሄድ የሚያጠፉትን ጊዜና ገንዘብ ለማስቀረት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ጉባኤው የሚቋቋመውም በተካራካሪ ወገኖች ስምምነት ሲሆን ተካራካሪዎቹ ባላቸው የመዋዋል ነፃነት ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የሚስማሙት ሁኔታ መኖሩ በራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ የተቋቋመው ጉባኤ በተገቢው ጊዜና በአነስተኛ ወጪ ጉዳያቸውን ለመወሰን ይችላል የሚል እምነት ኑሯቸው ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከቁጥር 315-319 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ይህንኑ የሚያስገነዝቡን ሲሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 350(2) በተለይ ሲታይ ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በሚሌ ለመስማማት መብት ያላቸው ስለመሆኑ ያስረዳናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ስምምነት ከተደረሰም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 356 ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች በስተቀር የጉባኤው ውሳኔ በፍርድ እንዲሻርላቸው ለመጠየቅ እንደማይችሉ ተደንግጓል፡፡ ይህ ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ ስምምነት ያላቸው ከሆነ የሚፈፀም ስነ ስርዓት ሲሆን ስምምነት ባይኖርም ይግባኝ የሚቻለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 351 ስር በተመለከቱት ውስን ምክንያቶች ብቻ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 351ም ሆነ 356 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለው የግልግል ጉባኤ ውሳኔ በሰበር ስርዓት የሚታይበት አግባብ ስለመኖሩ አይጠቁምም፡፡ በሌላ አገላለፅ ድንጋጌዎቹ የሚያወሱት በግልግል ታይቶ የተወሰነ ጉዳይ በይግባኝ የሚታይበትን ሥርዓት ብቻ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ድረስ በተመለከቱት ዴንጋጌዎችና በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ለመጨረስ መሰረቱ ሕጋዊ ውል መኖሩ ሲሆን ውል ደግሞ የተከራካሪ ወገኖች መብትና ጥቅም ማስገኛ ምንጭ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ውል መብትና ጥቅም የሚሰጠው ለተዋዋይ ወገኖች ወይም መብትና ጥቅሙ በሕጉ አግባብ ለተላለፈላቸው ለሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ነው(የፍ/ህ/ቁጥር 1731 እና 1957 ይመለከል)፡፡ እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ ለመጨረስ መብት ያላቸው መሆኑ በሕጉ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ሕጉ ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ ያላቸውን ሚናም ደንግጓል፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች በ1952ቱ የፍትሐ ብሔር ሕግና በ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርአት ሕጋችን ውስጥ ያሉት ሲሆኑ ከእነዚህ ሕግጋት በኋላ የወጡት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስትና አዋጅ ቁጥር 25/1988 እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 454/97 ስለሰበር ሥርዓት ደንግገው እናገኛለን፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ስልጣን ያለውና የሚሰጠው የሕግ ትርጉምም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት እስካልተለወጠ ድረስ የፌዴራሉንም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶችን የሚያስገድድ መሆኑ በሕጉ የተቀመጠና አላማው በአገሪቱ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎምና አፈጻጸም እንዲኖር ማረጋገጥ ነው ከተባለ ተከትሎ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ከሆኑት አንዱ በሆነው በግልግል ዳኝነት (arbitration) ጉዳዩ ቢታይና ይኸው አካል በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የሌለው የመጨረሻ ስለመሆኑ (Arbitration Finality Clause) ተከራካሪ ወገኖቸ ገልፀው ስምምነት ቢያደርጉ ጉዳዩ በሰበር ሊታይ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ይኸው ጥያቄም ስለሰበር ሥርዓት አላማና ከሕጎቹ አወጣጥ ቅደም ተከተል እንዲሁም በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ፍርድ ቤቶች በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ላይ ካላቸው ሚና አንፃር ታይቶ ምላሽ የሚሰጠው ነው፡፡ በዚህም መሰረት

ከላይ እንደተመለከተው የሰበር ሥርዓት ዓላማ ወጥ ለሆነ የሕግ ትርጉም እና አፈፃጸም ከፍተኛ ሚና መጫወት ሲሆን ይህንንም በ1987ቱ ሕገ-መንግስትም ሆነ ይህንኑ ተከትለው ከወጡ አዋጆች(25/1988 እና 454/97) የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ እነዚህ አዋጆች ከ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በኋላ የወጡ ሲሆን ተቀባይነት ባለው የሕግ አተረጓጎም ደንብ መሰረትም ከ1958ቱ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ቅድሚያ ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው፡፡ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች በኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሲሆን እነዚህን የሙግት መፈቻ ዘዴዎች ፍርድ ቤቶች የሚያበረታቱበት ሁኔታ እንዳለ ሁሉ የሚቆጣጠሩበት አጋጣሚም ያለ መሆኑን ከላይ የተመለከቱት የፍትሐ ብሔር ሕጉም ሆነ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የአንድ ጉዳይ ለሰበር የመቅረብ ሁኔታ በሕገ መንግስቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ በመሆኑ ሥርዓቱ ሊጫወተው ከተፈለገው አቢይ አላማ አንፃር ሲታይ ጉዳያቸው በግልግል ዳኝነት እንዲታይላቸው የተስማሙ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው በማለት ስለተስማሙ ብቻ ጉዳዩ በሰበር ሥርዓቱ እንዳይታይ ፍላጎት አሳይተዋል ተብሎ መሰረታዊውን የሕግ ስህተት ላለማረም ምክንያት ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21849 በቀረበው ጉዳይ ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት(Arbitration) ለመጨረስ ከተዋዋለና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በማለት በውላቸው ላይ ከተስማሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ አይገባም በማለት የሠጠው ውሳኔ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(4) መሰረት መለወጥ ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ በሰበር ችልት ሊቀርብና ሊታይ የሚገባ አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

**2.ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**

ተጠሪ ውሉን ማቋረጡን ሳይክድ የሰላሳ አምስት ቀናት ቅጣት አመልካች እንዲከፍለው ዳኝነት የጠየቀውንና የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ውሳኔ ያሳረፈው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በጥር 23 ቀን 1998 ዓ/ም የወርቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ውል ተፈፅሞ፣ቅድሚያ ክፍያ በየካቲት 09 ቀን 1998 ዓ/ም ተከፍሎ ስራው መጀመር ከሚገባበት ቀን ሰላሳ አምስት ቀናት በመዘግየት በ30-7-1998 ዓ/ም ለመጀመሩ ምክንያት አመልካች ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ነው፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ገልፆ የሚከራከረው የማዕድን ፍለጋ ጉድጓድ ቁፋሮ ወደሚካሄድበት ቦታ የሚያደርሰውን ለተሽከርካሪ እንቅስቃሴ አመቺ የሆነ መዳረሻ መንገድ የማዘጋጀት ኃላፊነት የራሱ መሆኑ በውሉ መገለጹን ሳይክድ ይህንኑ ግዴታ ለመወጣት ቡልዶዘሩን ከተጠሪ መከራየቱን፣ሆኖም በሁለት ቀናት ውስጥ ቡልዶዘሩን ወደ መቀሌ ለማጓጓዝ የሚያስችል መኪና አዘጋጅቶ ለማስጫን በሚሄድበት ጊዜ የቀረበው ቡልዶዘር ለታቀደው ስራ ብቃት የሌለው መሆኑ በአመልካች ኤክስፐርት በመረጋገጡና ይህ ሁሉ ሲደረግ ተጠሪ የወሰዱት አንዳችም እርምጃ የለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክር የአመልካች ክርክር በስር የግልግል ዳኝነት ያልተነሳ ነው በማለት ከመከራከር ውጪ ከላይ የተመለከተው ግዳታ በግራ ቀኙ መካከል መገባቱን በግልፅ አይክድም፡፡ ይሁን እንጂ

አመልካች በስር የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ከላይ የተመለከተውን ክርክር ያነሳ መሆኑን የግልግል ጉባኤ ውሳኔ ግሌባጭ በገጽ 3 እና 4 ያሰፈረው በመሆኑ ተጠሪ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1)መሰረት በማድረግ ያነሳው ተቃውሞ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ውድቅ ሆኖ ለሰላሳ አምስት ቀናት የቅጣት ገንዘብ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ስንመለከተው ደግሞ ምላሹ ከግራ ቀኙ ውል፣ክርክርና ስለውሎች አተረጓጎም በጠቅላላው በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጥር 23 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው ውል አመልካችን ለባከነ ጊዜ ክፍያ ኃላፍነት ያለበት ስለመሆኑ በአንቀጽ 4፣3.11 እና 9.1 ስር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች እንገነዘባለን፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች ለተጠሪ ኃላፊነት የሚኖረው የመቆፈሪያው መሳሪያ ከአመልካች ጋር በተያያዘ ኃላፊነት ያለስራ ቢቀመጥ ስለመሆኑ ተቀምጧል፡፡ ድንጋጌዎቹ በግልፅ እንደሚያሳዩት የባከነ ጊዜ ክፍያ(Idle time Payment) የመቆፈርያው መሳሪያ በስራ ላይ እያለ ውል ሰጪ በሆነው አመልካች ምክንያት ቢቆም፤መሳሪያው ስራ ለመስራት እየቻለ ቁሞ ያላግባብ ለጠፋው ጊዜ፣አመልካች ኃላፊ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በሌላ አገላፅ የመቆፈርያ ማሽን(Rig) በስራው ቦታ ላይ ተገኝቶ በአመልካች ምክንያት ስራ ቢፈታ አመልካች ኃላፊነቱን የሚወስድ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለሰላሳ አምስት ቀናት ስራ ፈታሁ ይበል እንጂ በአመልካች ምክንያት ስራ መፈታቱን በፍሬ ነገር ደረጃ አልተረጋገጠም፡፡ ተጠሪ ስራውን የፈታሁ በአመልካች ምክንያት ነው ብሎ እስከተከራከረ እና አመልካችም ለመሳሪያው መቆም ምክንያት የሆነው ድርጊት በራሱ በኩል የተፈጸመ አለመሆኑን ገልፆ እስከተከራከረ ድረስ ክሱን የማስረዳት ሸክም ከሳሽ የሆነው ወገን የተጠሪ ግዴታ ነው፡፡ የመቆፈሪያው መሳሪያ ከስራ ቦታ አለመድረሱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የግልግል ጉባኤው አመልካችን መሳሪያው ስራውን ለፈታበት ጊዜ ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ላይ የደረሰው ከላይ የተጠቀሱትን የውሉን ድንጋጌዎች በመጥቀስና መቆፈርያ መሳሪያ ወደ ስራ ቦታ ተጓጉዞ የሚሄድበትን መንገድ አመልካች ሊያዘጋጅ አልቻለም፣የዶዘር ኪራይ ውሉን መሰረት በማድረግ ክስ አልመሰረተም በሚል ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ ስራውን ከሚያዚያ 01 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ መስራት እንደሚችል በፁሁፍ ተነግሮት ሚያዚያ 12 ቀን 1998 ዓ/ም ስራው መጀመሩ፣የሰላሳ አምስት ቀናት ጊዜ ባክኗል የተባለው ደግሞ ከየካቲት 24 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 30 ቀን 1998 ዓ/ም ድረስ ስለመሆኑ በስር ክርክር የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የመቆፈሪያ ማሽኑ ወደ ስራ ቦታው በመሄድ በአመልካች ምክንያት ስራውን መስራት ያልቻለ መሆኑን ሳይሆን ከመነሻውም መቆፈሪያ ማሽኑ ወደ ስራ ቦታ ያልተጓጓዘ መሆኑን ነው፡፡በግራ ቀኙ ውል አንቀፅ 3.11 ስር የተቀመጠው ድንጋጌ የመቆፈሪያ መሳሪያ ከአሰሪው ጋር በተያያዘ ኃላፊነት ያለስራ ቢቆም....በሚል ሐረግ የተቀመጠ ሲሆን ይህም ድንጋጌ በግልጽ መሳሪያው ከስራ ቦታ መድረሱንና ደርሶ ስራ መስራት እየቻለ በአመልካች ምክንያት ስራውን ሳይሰራ ቢቀር አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ግልፅ ውል ሊተረጎም የማይገባ መሆኑን ደግሞ የፍ/ብ/ሔ/ቁጥር 1733 ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ የግልግል ጉባኤ ውል ግልፅ ሆኖ እያለ እና ተጠሪ አመልካች ለባከነው ጊዜ ምክንያት መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ የተጠሪን የማስረዳት ሸክም ወደ አመልካች በማዞር አመልካች ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የደረሰበት መሆኑን አላስረዳም በማለት ለባከነ ጊዜ ቅጣት እንዲከፍሉ ሲል የሠጠው የውሳኔ ክፍል የግራ ቀኙን ክርክርና የውል ይዘት በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች

ስለማስረዳት ሽክም የተቀመጡትን ሥርዓቶች፣በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 1732 እስከ 1738 ድረስ ስለውሎች አተረጓጎም ከተመለከቱት ደንቦች ጋር ያላገናዘበና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም አመልካች መቆፈሪያ ማሽኑ ስራ ሳይሰራ በመቆሙ ምክንያት ባከነ ለተባለው ለሰላሳ አምስት ቀናት ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር የሚከፈልበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የተሰሠጠው የውሳኔ ክፍል ሊለወጥ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪ በውሉ መሰረት ለተከናወኑ ስራዎች መከፈል አለባቸው ተብለው የታሰቡት፤ የሞቢላይዜሽን ሂሳብ( ብር 90,000.00)፣ ለ661.77 ሜትር ጥልቀት ጉድጓድ ቁፋሮ ሂሳብ(ብር 704,124.00)፣ ለኬዚንግ ስራ(ብር 138,000430.00)፣ ለቁፋሮ ስራ ከጉድጓድ ወደ ጉድጓድ ለተደረገ እንቅስቃሴ የሚታሰብ(ብር 4,150.00)፣ስራ ላይ ለዋለ አምስት ከረጢት ሲሚንቶ የሚታሰብ(ብር 750.00)፣ከውሃ ቦቴ ኪራይ የሚታሰብ(50,000.00)እና የዶዘር ኪራይ(ብር 3,818.40) በጠቅላላ ድምር ብር 991,272.40(ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከአርባ ሳንቲም) ተጨማሪ እሴት ታክስ ተጨምሮበት ብር 1,139,962.86 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ስላሳ ሁለት ብር ከሰማኒያ ስድስት ሳንቲም)እንዲከፍል የተወሰነውን የውሳኔ ክፍል ስንመለከተው በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ውል፣ ክርክርና ማስረጃ መሰረት አድርጎ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች የሰበር ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አመልካች ክፍያ ለዘገዬበት ብር 40,321.60(አርባ ሺህ ሶስት መቶ ሃያ አንድ ብር ከሰላሳ ሳንቲም) ለተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑም ፍሬ ነገርን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው ባለመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው አመልካች ተጠሪ ውሉን በራሱ ጊዜ አቋርጦ መሄዱ ያላግባብ ነው በማለት በተከሳሽ ከሻስነት በግልግል ጉባኤው ያቀረበው ክርክር የታለፈው ባግባቡ አይደለም በማለት የሚከራከርበትን ነጥብ ስንመለከተውም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1786 እና 1788 ድንጋጌዎች አንጻር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ በግልግል ጉባኤ ታይቶ በሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን አንድ ተከራካሪ ወገን ቢስማማም ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ቅሬታውን ለሰበር ችሎቱ ከማቅረብ የሚከለከል ባለመሆኑና ጉባኤው አመልካች የሰላሳ አምስት ቀናት መቆፈሪያው ያለስራ ለቆመበት አመልካችን ተጠያቂ ያደረገበት አግባብ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ፣ እንዲሁም ጉባኤው ወጪና ኪሳራ ያሰላበት አግባብ ይህ ችሎት ለአመልካች የሚቀንሰውን የገንዘብ መጠን መሰረት ባደረገ መንገድ የሚሰራ ሆኖ በሌሎች ነጥቦች ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሣኔ**

1. ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21849 በቀረበው ጉዳይ ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት (Arbitration) ለመጨረስ ከተዋዋለና የግልግል ዳኝነት

ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በማለት በውላቸው ላይ ከተስማሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ አይገባም በማለት የሠጠው ውሳኔ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(4)መሰረት ተለውጧል፡፡

2. ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት(Arbitration) ለመጨረስ ከተዋዋለና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በማለት በውላቸው ላይ ከተስማሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ የሚችል ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ የሰላሳ አምስት ቀናት ቅጣት የተባለውን ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ ለመክፈል የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት በዚህ ረገድ የግልግል ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ሽረነዋል፡፡
4. ወጪና ኪሳራን በተመለከተ የግልግል ጉባኤው የሰጠው የውሳኔ ክፍል አመልካች ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በዚህ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ግንዛቤ ባስገባና በጉባኤው ስሌት መሰረት የሚሰራ ሁኖ በወጪና ኪሳራ፣በጠበቃ አበል እንዲሁም በሌሎች ነጥቦች ላይ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 37678

ኅዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብድልቃድር መሃመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዒሊ መሃመድ

አመልካች፡- ድራጋዶስ ጄ ኤንዴ ፒ. ጆየንት ቬንቸር - ጠበቃ አቶ ዱቻ ፈለቀ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሳባ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኅበር ጠበቆች

1. ሲራጅ አብደላ

2. ድልነሣው ታደሰ አቶ ኒቆድሞስ ጌታሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥል የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ጉባዔ ከተሰጠ ውሣኔ ጋር በተያያዘ የይግባኝ አቀራረብን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥን እንደተመለከትነው አመልካች ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር ከአዲስ አበባ እስከ ጅማ ድረስ ያለውን አውራ መንገድ የማሻሻያና መልሶ ጥገና ሥራ ለመሥራት ውል ተዋውሎ ከመንገድ ሥራ የተወሰነውን በንዑስ ሥራ ተቋራጭ /sub- contract/ ውል ለማሰራት በነበረው ፍላጎት ከተጠሪ ጋር የካቲት 25 ቀን 1996 ዓ.ም የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውል እንደተዋዋለ በዚህም የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውል አንቀጽ 17 ላይ በውሉ አፈፃፀም ረገድ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር በአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሥር በተቋቋመው የግልግል ተቋም ታይቶ እንድሚወሰን በተስማሙት መሠረት በክፍያ አፈፃፀም ረገድ በመካከላቸው አለመግባባት በመፈጠሩ ተጠሪ አቤቱታውን ግራ ቀኙ ለመረጡት የግልግል ተቋም አቅርቦ ተቋሙም በሚሰራበት የግልግል ደንብ /rules of procedure/ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ የካቲት 3 ቀን 1999 ዒ.ም ውሣኔ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡

ከዚህ በኋላም የሥር ተከሣሽ የአሁን አመልካች የግልግል ጉባዔው በሰጠው ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባይ ይግባኝ ያቀረበው ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ምክንያት ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ ጉዳዩን በመመርመር አለመግባባቱ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ አስቀድሞ ግራ ቀኙ እንደተስማሙ፣ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት የተመለከተውም ተቋም በአዋጅ ቁጥር 341/95 መሠረት ሥልጣን በተሰጠው አካል እንደተቋቋመ፣ ይግባኝ ባይ ጉባዔው ጉዳዩን እንዲመለከት ከፈቀደ በኋላም በክርክሩ ሂደት ሙሉ በሙሉ እንተካፈለ፣ የግልግል ጉባዔው የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ እንደሌለውም የግልግል ጉባዔው በሚመራበት ደንብ ላይ እንደተመለከተና ይግባኝ ባይ ይህ የደንቡ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ቢከራከርም ግራ

ቀኙ ወገኖች ወደ ግልግል ተቋሙ ሲሄዱ ተቋሙ ክርክሩን የሚመራበት የእራሱ ሥርዓት እንዳለው ስለሚታወቅ ይግባኝ ባይ በተቋሙ በመዳኘት እስከመረጠ ድረስ በተቋሙ አሠራር የማይገዛበት ምክንያት ስለሌለ በዚሁ መሠረት በግልግል ውሣኔው ላይ ይግባኝ አይባልበትም ተብሎ በግልግል ደንቡ ላይ የተቀመጠውን እንደተቀበለው ስለሚቆጠር በዚህ ረገድ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የይግባኝ መብቱን ቀሪ ባደረገበት ሁኔታ ስለሆነ አግባብነት የለውም በማለት ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ሰበር ችሎቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የግልግል ተቋሙ የሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይባልበት ነው መባሉ ተጠሪ ባለበት ለሰበር ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍና በቃል አከራክሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የግልግል ተቋሙ የሚመራበትን የሥነ-ሥርዓት ደንብ /rules of procedure/ እና እንደዚሁም በግራ ቀኙ ወገኖች የተደረጉ የተለያዩ መፃፃፎችን ለጉዳዩ አወሳሰን እንደሚረዳ በማመኑ ችሎቱ አስቀርቦ ተመልክቷቸዋል፡፡

የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥም አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ይግባኝ የሚባልበት ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪ የካቲት 25 ቀን 1996 ዓ.ም የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውል ሲዋዋል በውሉ አፈፃፀም ረገድ አለመግባባት ሲፈጠር ይሄው አለመግባባት በአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሥር በተቋቋመው የግልግል ተቋም ታይቶ እልባት እንደሚያገኝ መስማማታቸውን የተገነዘብን ሲሆን ይህን ተቋም /forum/ በመምረጥ ረገድ ስምምነት ስለመድረሱ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የግልግል ተቋሙን በመምረጥ ረገድ በመካከላችን ስምምነት ቢኖርም የግልግል ተቋሙ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ ግራ ቀኛችን አልተስማማንም፡፡ የግልግል ተቋሙ የሚመራበት የግልግል ደንብ ላይ የጉባዔው ውሣኔ ይግባኝ እንደማይባልበት ቢጠቀስም ይህ የደንቡ ቃል በሕገ መንግሥት የተረጋገጠን የይግባኝ መብትን የሚፃረር ከመሆኑም በላይ የግልግል ዳኞች በሚሰጡት ውሣኔ ላይ ከፍ/ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይቻላል ተብሎ በፍ/ብ//ሥ/ሥ/ሕ. ቁ. 350/1/ ላይ የተመለከተውንም የሚጋፋ ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ነው፡፡

ተጠሪም በበኩሉ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውሉ መሠረት የተፈጠረውን አለመግባባት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ም/ቤት ሥር ለተቋቋመው የግልግል ዳኝነት ተቋም አቤቱታው ሲቀርብ ጉባዔው የተጠሪን ክስ እንደዚሁም የግልግል ተቋሙ የሚመራበትን ደንብ ለአመልካች በሸኚ ደብዳቤ እንዲላክና አመልካችም ስለደንቡ አንዳንድ ማከራከሪያ ከጠየቀ በኋላ ተቀብሎ የግልግል ጉባዔውን የተለያዩ ድንጋጌዎች በመጥቀስ የተከራከረ ሲሆን ይህም አመልካች ደንቡን ተቀብሎ ሙግቱን መቀጠልን የሚያሣይ ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በደንቡ ለመግዛት ሙሉ ፈቃድን ስለሰጠ የጉባዔው ውሣኔ ይግባኝ አይባልበትም ተብሎም በዚሁ ደንብ ላይ የተጠቀሰውንም እንደተቀበለው ይቆጠራል በማለት ይግባኙን ሣይቀበል መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችና ተጠሪ አለመግባባትን በግልግል ለመፍታት በውል የመረጡት የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም የሚመራበት የግልግል ደንብ የውል ክርክርን ለግልግል ስለማቅረብ

በሚደነግገው አንቀጽ 1/1/ ሥር ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን በሚመለከት ለሚነሱ ማናቸውም አለመግባባቶችና ክርክሮች በአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት የግልግል ተቋም የግልግል ደንብ ውሣኔ እንዲያገኝ በጽሁፋቸው ሲስማሙ በዚሁ መሠረት እነዚህ አለመግባባቶች በተቋሙ የግልግል ደንብ ውሣኔ እንደሚሰጣቸው መደንገጉን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ የግልግል ደንብ አንቀጽ 1/1/ ላይ እንደተመለከተው ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ወደዚህ የግልግል ተቋም ሲሄድ የግልግል ተቋሙ ግራ ቀኙን ማከራከር ከመጀመሩ በፊት ተከራካሪ ወገኖች በዚህ የሥነ-ሥርዓት ደንብ የሚይዙ ስለመሆኑ የጽሁፍ ስምምነት መቀበሌ እንደሚገባው አከራካሪ አይሆንም፡፡

በእርግጥ የግልግል ጉባዔው ተጠሪ ያቀረበውን ክስና የግልግል ተቋሙም የሚመራበትን ይህንኑ የግልግል ደንብ አያይዞ ለአመልካች እንደላከበና አመልካችም ይህንኑ ደንብ መሠረት አድርጎ ክርክሩን መምራቱን መገንዘብ ቢቻልም ሁኔታው ደንቡን ካወጣው ተቋም ሃሣብ /intention/ አንፃር ሲታይ ደንቡን ጠቅላላ ድንጋጌ ተከራካሪ ወገኖች ተገንዝበው በዚሁ መሠረት ለመገዛት ወስነዋል ለማለት የሚቻለው በደንቡ አንቀጽ 1/1/ ላይ እንደተመለከተው ግልጽ የሆነ የጽሁፌ ስምምነት ሲኖር ነው፡

በሌላ በኩልም አመልካች ደንቡ ደርሶት የደንቡንም የተለያዩ ድንጋጌዎች በመጥቀስ ሙግቱን የቀጠለ ስለሆነ ደንቡን እንደተቀበለውና በዚሁ ደንብ አንቀጽ 20/2/ መሠረትም የይግባኝ መብቱን እንደተወ ይቆጠራል ቢባል እንኳን ይግባኝ መሠረታዊ መብት እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ መሠረታዊ መብት ተፋላሚ ወገኖች አስቀርተዋል ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚገባ በተገነዘቡ ጊዜ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 350/2/ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን አስቀርተዋል ወይንም ትተዋል ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሙሉ በተረዱበት ደረጃ እርስ በርሣቸው በሚያደርጉት ስምምነት ሲሆን ነገር ግን አለመግባባቱ በግልግል ተቋሙ አማካይነት እንዲታይ ጥያቄው በቀረበ ጊዜ /at the stage of submission/ የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚገባ ተገንዝበዋል ለማለት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ናቸው ስለማይባል በዚህ ሁኔታ ይግባኙን ለማስቀረት የሚሰጡት ፈቃድ በሕጉ ላይ እንደተቀመጠው የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚገባ በመገንዘብ እንዳደረጉት የሚቆጠር አይሆንም፡፡

በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተመሥርተው ማብራሪያ የፃፉትም ፕሮፌሰር አለን ሴድለር ይህንኑ በማብራሪያቸው ላይ አንፀባርቀውታል፡፡

አመልካች የይግባኝ መብቱን ለመተው አድርጎታል የተባለው ስምምነት የነገሮችን አካባቢ ሁኔታዎች በሚገባ ካለመገንዘብ ነው ከተባለ ደግሞ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 350/2/ ድንጋጌ መሠረት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው ማለት ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የይግባኝ መብቱን ያስቀረ ስለሆነ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ሣይቀበለው መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 29612 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የይግባኝ መብቱን ቀሪ ያላደረገ ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን መርምሮ የበኩሉን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 30727

ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጐስ ወልዱ
ታፈሰ ይርጋ
መድኅን ኪሮስ
አልማው ወሌ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ/ማኅበር ነ/ፈጅ ወንድአንተ ነጋሽ

ተጠሪ ፡- ጄቲቲ ትሬዲንግ ሥራ አስኪያጅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ግራ ቀኞችን ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረግነው ውል ከከሳሽ ጋር 10 ኢንች የማይዝግ የብረት ቧንቧ ለማቅረብ ስምምነት የተደረሰ ቢሆንም ተከሳሽ ውሉን በማፍረሱ ያለመግባባት በመፈጠሩ ምክንያት ችግሩን ለመፍታት ከሳሽ የበኩሉን ጥረት ቢያደርግም በተከሳሽ በኩል አዎንታዊ ምላሽ ባለመገኘቱ በውሉ አንቀጽ 10/4/ /2/ መሠረት ጉዳዩን በግልግል ለማየት ተጠሪ የግልግል ዳኛ በ10 ቀን ውስጥ መርጦ እንዲያሳውቀን በጽሁፍ ያሳወቅነው ቢሆንም ፈቃደኛ ያልሆነ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በተከሳሽ ምትክ በሕግና በውላችን መሠረት የግልግል ዳኛ እንዲመርጥልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ አቤቱታም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በሕግም ሆነ በኩባንያው የመመስረቻ ጽሁፍ፤ በመተዳደሪያ ደንቡ እንደዚሁም በሥነ ሥርዓትና በፍ/ብሔር ሕጉ የተቀመጠው የችሎታ መስፈርት ለተጠሪው ወይንም ለእንደራሴው አልተሰጠም ብለዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ተከሳሽ የግልግል ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በእራሳቸው የግል ችሎታ ሳይሆን በሌሎች
የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰዎች ስም የሆነ እንደሆነ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ እንዲስማሙ የሚያስችላቸው ልዩ የውክልና ስልት እንዲኖራቸው ይገባል ያሉ ሲሆን አመልካች ወደ ግልግል ዳኝነት እንግባ የሚልበት ጉዳይ በግልግል ስምምነቱ አይሸፈንም እንጂ የሚሸፈን ነው ቢባል እንኳ ወደ ግልግል ዳኝነት ከመግባቱ በፊት በእራሳቸው በተዋዋዮች ድርድር ተጀምሮ በሂደት ላይ ያለው ስምምነት ገና ያልተጠናቀቀ ስለሆነና ይህንንም ለማድረግ ውሉ ስለሚያስገድድ በዚህ ሁኔታ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተገቢነት ያለውን የክርክሩን ጭብጥ ከያዘ በኋላ ተጠሪ የአክሲዮን ማኅበር ሲሆን ተጠሪና አመልካች ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተዋዋሉት መሠረት ያለመግባባቶችን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት ተደርጐ ካልተቻለ የግልግል ዳኛ
በመምረጥ ጉዳዩ እንደሚታይ የተስማሙ ስለሆነ አክሲዮን ማኅበር ያለመግባባቶችን በግልግል ለመፍታት እንደማይችል የሚያመለክት የሕግ ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ጉዳዩን በግልግል መጨረስ አልችልም በማለት ያቀረበው ክርክር አግባብነት የሌለው ነው ካለ በኋላ የተፈጠረውን ያለመግባባት በውሉ መሠረት በስምምነት ለመፍታት ከሳሽ /አመልካች/ ተገቢውን ጥረት ስለማድረጉ ካቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ግራ ቀኙ ያለመግባባታቸውን በስምምነት

መጨረስ ስላልቻሉ ጉዳያቸው በግልግል ዳኛ አማካይነት መታየት ስላለበት የየበኩላቸውን የግልግል ዳኛ መርጠው ይቅረቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሥር ተከሳሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በግልግል ዳኛ እንዲታይ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነቱ ተጠሪ ባለበት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የዚህን ችሎች ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጥሯል የተባለው አለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ሊታይ ይችላል ወይንስ አይችልም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን መርምረናል፡፡

በቅድሚያም አመልካች ምን ዓይነት የሕግ ሰውነት (legal personality) እንዳለው መመልከት ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ሲታይ አመልካች የአክሲዮን ማኅበር እንደሆነ ከክርክሩና ከቀረበው ማስረጃ ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን ይህንንም የሕግ ሰውነት ማግኘት የቻለው አስቀድሞ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደነበረና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/91 መሠረት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አንድን የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኅበርነት እንዲለወጥ ማድረግ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 5/1/ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ መሠረት አመልካች ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተቀየረ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ መልኩ የሚቋቋሙና በንግድ ሕጉ መሠረት የሚቋቋሙ የአክስዮን ማኅበራት በአክሲዮን ባለቤትነት በሥልጣንና በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ አንድ ዓይነት እንዳልሆኑ ከተጠቀሰው አዋጅ መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ የንግድ ሕግ ቁጥር 307/1/፣ 311፣ 312/1/ለ/፣ 315፣ 347/1/ እና 349 ከመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኅበርነት በተለወጡት ላይ ተፈፃሚነት እንደሌላቸው ነገር ግን ሌሎች የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በአዋጁ ላይ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት የአክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊኖረው እንደሚችል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 348/3/ ላይ የተመለከተ ሲሆን በተያዘውም ጉዳይ አመልካች አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ያለው ስለመሆኑ በአክሲዮን ማኅበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የተመለከተ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩልም የአመልካች አክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 ሥር የተዘረዘሩ ሲሆን ተጠሪም በዚሁ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12/2/ ሥር ዋና ሥራ አስኪያጁ የኩባንያውን የእለት ተእለት ሥራ ያከናውናል ተብሎ የተመለከተው ከሌሎች ወገኖች ጋር ውል መዋዋልን በውሉ አፈፃፀም ረገድ ያለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩን በግልግል ለማየት መስማማት እንደሚችልም ስለሚያስገነዝብ በዚሁ መሠረት ውሉ የተፈረመ ስለሆነ ጉዳዩ በግልግል እንዲታይ መወሰኑ አግባብነት አለው በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁንና ዋናው ሥራ አስኪያጅ የኩባንያውን የእለት ተእለት ሥራዎች ያከናውናል ተብሎ ሥልጣንና ተግባሩን በሚዘረዝረው የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም አክሲዮን ማኅበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ ሲታይ ሙሉ በሙሉ በንግድ ሕጉ መሠረት ያልተቋቋመ ስለሆነና ዋናው ሥራ አስኪያጁ ኩባንያውን በመወከል ውል የመዋዋል ሥልጣን እንዳለው መገንዘብ ቢቻልም ከዚህ አልፎ በውሉ አፈፃፀም ረገድ ያለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩ

በግልግል ዳኛ አማካይነት እልባት እንዲያገኝ ለመስማማት እንደሚችል ሥልጣን ያልተሰጠው መሆኑን መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት መታየት ይችላል በማለት የሰጡት ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 146/91 እና ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ጋር ያልተጣጣመ በመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 59068 በየካቲት 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 46254 በየካቲት 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተቋቋመበት ሕግ አኳያና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ዋናው ሥራ አስኪያጅ በውል አፈፃፀም ረገድ የሚፈጠርን ያለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት እልባት እንዲያገኝ ለመስማማት ሥልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጥሯል የተባለው ያለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ሊታይ አይችልም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡